# ቃለመጠይቅ / የታሪክ ፈቃድ ፎርም

## ስለ ድርጅታችን

የልጆች የህግ ማእከል (Children's Law Center) በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ ያለ እያንዳንዱ ልጅ ፤ የተረጋጋ የቤተሰብ ህይወት፣ ጥሩ ጤንነትና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ ለማረጋገጥ ላለፉት 25 ዓመታት ሲታገል ቆይቷል።

## መብቶችዎ

**1. በዚህ ቃለመጠይቅ፤ ስእል ወይም ቪድዮ ፕሮጀክት መካፈል <u>በፍቃደኝነት የሚደረግ ነው</u>**

ተሳትፎዎ ሙሉ በሙሉ በእርሶ ፈቃደኝነት ላይ የተመረኮዘ ነው። ቃለመጠይቅ እንድናደርግሎ፣ ፎቶ ልናነሳ።ዎት ወይም በቪድዮ እንድንቀርጾት ካልፈለጉ የግድ መስማማት የለቦትም። የእርሶ እሺ ወይም እምቢ ማለት ከዚህ የልጆች የህግ ማእከል (Children's Law Center ) በአሁኑ ግዜም ሆነ ወደፊት የሚያገኙትን አገልግሎት የሚነካ አይደለም።

**2. <u>በማንኛውም ግዜ</u> የጀመሩትን ቃለመጠይቅ፣ ስእል ወይም የቪድዮ ማንሳት ተግባር የማስቆም መብት አሎት።**

ቃለመጠቁን በማድረግ ላይ እያለን ወይም ስ እሎን በምንወስድበት ግዜም ሆነ በቪድዮ እያቀረጽኖት እያለን በማህል አቁሙ ብለው ሊያቋርጡን ይችላሉ። ለምን አቁሙ እንዳሉን ደግሞ ምክንያት መስጠት አያስፈልጎትም።

**3. የሰጡንን ስልጣን/ፈቃድ መልሶ የማንሳት መብት አሎት።**

የሰጡንን ፈቃድ መልሰው ለመውሰድ ከፈለጉ ወደ ካት ሉጎ ( *Kat Lugo* ) በ *[klugo@childrenslawcenter.org](mailto:klugo@childrenslawcenter.org) ኢሜል መጻፍ ይችላሉ ወይም በስልክ ቁጥር* (202) 467-4900 ደውለው የግንኙነት ዳይሬክተሩ እንዲቀርብሎት ይጠይቁ።

## ስለ ፕሮጀክቱ፡

ከእኛ ጋር ቃለመጠይቅ እንዲያደርጉና ታሪኮን ከሌሎች ጋር እንድንካፈል እንዲፈቅዱልን እንጠይቃለን። ከእርሶ ጋር ቃለመጠይቅ በምናደርግበት ግዜ፤ የግሎን መረጃ ሊያካፍሉን ይችላሉ። ይህ ቃለመጠይቅ፤ ከ ልጆች የህግ ማእከል (Children's Law Center) ከሚያገኙት አገልግሎት ጋር የተያያዘ አይደለም። እርሶ የሚሰጡንን መረጃ ከሌሎች ጋር እንድንካፈለው ፈቃድዎን በመጠየቅ ላይ የምንገኘው የእርሶ ተመክሮ ፤ የዲሲ ወላጆችና ልጆች የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች ስለሚገልጽ፤ የሰውን ንቃተ-ሂሊና ከፍ ለማድረግና ሰው እገዛውን እንዲያበረክት ለማድረግ ነው። በዚህም አንድነታችንን ካስተባበርንና ካጠናከርን በልጆች ህይወት ላይ ለውጥ ለማምጣት እንደሚያግዘን ሌሎች ሰዎች እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

እንደ አንድ የቃለመጠይቁ አካል ፤ ከዚህ የሚቀጥለውን እናደርጋለን፡

- ☐ የእርሶን ፎቶ/ስእል እናነሳለን
- ☐ ድምጾን እንቀዳለን
- ☐ በቪድዮ እንቀርጾታለን

### የእርሶን ታሪክ እንዴት ነው ከሌሎች ጋር መካፈል የሚቻለው ?

1. ታሪኮን ለምን ዓይነት ጉዳይ ብንካፈለው ነው የሚመርጡት? (የሚፈልጉት ላይ ምልክት ያድረጉ )
   - ☐ ገንዘብ ለማዋጣት፤ ድርጅታችን ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የገንዘብ መዋጮ ስንጠይቅ
   - ☐ መስበክ (Outreach)፡ ሌሎች ሰዎች ስለ ድርጅታችን እንዲያውቁ ና ከአገልግሎታችን እንዲጠቀሙ ለማገዝ በምናካሂደው ገለጻ ወይም ስብከት
   - ☐ ለአቋማችን ጠበቃ ስንቆም፡ ልጆችን የሚመለከቱ ወይም ልጆችንና ቤተሰቦቻቸውን የሚጠቅሙ ህጎችና መመርያዎች እንዲተላለፉ በምንሰራበት ሁኔታ
2. የእርሶን ታሪክ በምን ላይ ብናወጣው ነው  የሚመርጡት?(ሚመለከቶት ላይ ምልክት ያድርጉ)
   - ☐ ታትሞ በሚወጣ ጽሁፍ (ለምሳሌ በፖስታ በሚላኩ ደብዳቤዎች)
   - ☐ በኦንላይን በሚዘረጉ ጽሑፎች (ለምሳሌ ዌብሳይት፣ ኢሜል)

☐ በመገናኛ ብዙሃን (ለምሳሌ በፌስቡክ (Facebook)፣ በትዊተር (Twitter)፣ በሊንክዲን (LinkedIn)

3. ስምን ልንገልጽ እንችላለን? (አንዱን ያክብቡ)

   አዎን ወይም አትችሉም

4. የልጅዎን/ልጆችዎን ስም ልንጠቀምበት እንችላለን? (አንዱን ያክብቡ)

   አዎን ወይም አትችሉም ወይም አይመለከትም (N/A)

5. ለ 3ኛና ወይም 4ኛ ጥያቄዎች የሰጡት መልስ "አትችሉም" የሚል ከሆነ ምን ዓይነት የብእር ስም (pseudonym) ብንጠቀም ይመርጣሉ? (እባኮን መልሶን ከወደታች ይጻፉ)

6. የነገሩን ታሪክ ከሌሎች ጋር በዚህ ዓይነት መንገድ እንደትካፈሉት አልፈልግም የሚሉት አለን? እንድናስተውለው የሚፈልጉት ሌላ ነገር አለን ? (እባኮን አስተያየቶን ከታች ባለው ባዶ ቦታ ይጻፉ) ።

## ፊርማ

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት፤ ይህንን ፎርም ሲፈርሙ የልጆች የህግ ማእከል (Children's Law Center) የሰጡትን መረጃ ከሌሎች ጋር እንዲካፈል ተስማምተዋል ማለት ነው። ይህ የፈቃድ ፎርም፤ የልጆች የህግ ማእከል (Children's Law Center)፣ ወኪሎቹና ሰራተኞቹ የእኔን ፎቶግራፍ እንዲያነሱ ወይም የህጋዊ አሳዳጊዬን፤ ወይም የልጆቼን፣ የንብረቴን ቪድዮ እንዲያነሱ/እንዲቀዱ ከላይ በተገለጸው መሰረት ታሪኬን ከሌሎች ጋር እንዲካፈሉ መብቱን እሰጣቸዋልሁ። በዚህም መሰረት የልጆች ህግ ማእከል (Children's Law Center)፤ ወኪሎቹና ዝውውሮቹ በጽሁፍ፣ በቪድዮ በኤሌክትሮኒክ መሳርያ ወይም በማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ታሪኬን እንዲያወጡ ስልጣኑን ሰጥቻቸዋለሁ።

| | |
|---|---|
| **የደንበኛ ስም** | **ፊርማ (ደንበኛ ወይም ስልጣን የተሰጠው ወኪል)** |
| **ቀን** | **የድርጅቱ ስም** |
| **ስልጣን የተሰጠው ወኪል ስም** | **ስልጣኑ ምን እንደሆነ ይግለጹ ( ለምሳሌ ወላጅ፣ አሳዳጊ)** |
| **ምስክር** | |